# ፖሊሲ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ
BOARD OF EDUCATION OF MONTGOMERY COUNTY

***ተዛማጅ ደንቦች፦*** ABC, ABC-RA, IOD-RA
***ኃላፊነት ያለው ቢሮ፦*** ዋና የአካደሚክ ኦፊሰር፣ የስርዓተ ትምህርት እና ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ጽ/ቤት፡
Office of the Chief Academic Officer; Office of Curriculum and Instructional Programs

## የእንግሊዝኛ ቋንቋን የማዳበር ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

A. **ዓላማ**

በአሁኑ ጊዜ የእንግሊዝኛ ቋንቋን የማዳበር (ELD) ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን እየወሰዱ ላሉ ወይም ቀደም ሲል ለወሰዱ ተማሪዎች የሚሰጥ ትምህርትን በተመለከተ ሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተማሪዎች ያለባቸውን ሃላፊነቶች ለማረጋገጥ፣

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) ለሚሰጥ ትምህርት ጠንካራ ጎኖችን እና ልዩነቶችን ያገናዘበ የትምህርት አቀራረብ ማዕቀፍ ለመመሥረት፣

EMLs ትምህርትን በተመለከተ የፌዴራል እና የስቴት መመሪያዎችና ህጎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ፣

B. **ጉዳዩ**

በቤታቸው ውስጥ ከእንግሊዘኛ ውጭ ሌላ ቋንቋ እየተጠቀሙ ያሉ ልጆች በትምህርት ቤት ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ወይም መድብለ ቋንቋ ተማሪ የመሆን እድል አላቸው። እነዚህ ተማሪዎች በቤት ውስጥ ቢያንስ አንድ ሌላ ቋንቋ እየተማሩ በተመሳሳይ ጊዜ/ጎን ለጎን እንግሊዘኛን ለመረዳት፣ ለመናገር፣ ለማንበብ እና ለመፃፍ እየተማሩ እንደሆነ እውቅና ለመስጠት ባለሙያዎች እነዚህን ተማሪዎች EMLs (ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች) በማለት ይጠሯቸዋል።

የእንግሊዝኛ ቋንቋን የማዳበር (ELD) ፕሮግራም ከአራቱ የቋንቋ ዘርፎች፣ ማለትም የአካደሚክ እና የማህበራዊ እንግሊዝኛን ማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብ፣ እና መጻፍ፣ በየትኛውም ዘርፍ ብቃትን ማዳበር ለሚፈልጉ በፌደራል ደረጃ ብቁ ለሆኑ EMLs (ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች) የተዘጋጀ ልዩ የትምህርት ፕሮግራም ነው።

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) የአስተሳሰብ፣ የባህል እና የባህርይ ልዩነቶችን በሜሪላንድ ውስጥ ላሉ ትምህርት ቤቶች አወንታዊ እሴቶች እንደሆኑ አድርጎ ይመለከታቸዋል። የሞንትጎመሪ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ABC፣ *የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ትብብርና ሊጋርነት፣* የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማህበረሰቦች በሁሉም MCPS ቤተሰቦች የተለያዩ ወጎች፣ማንነቶች፣ልምዶች፣እና ባህሎች የበለፀጉ መሆናቸውን እውቅና ይሰጣል። የአንድ ተማሪ የአፍ መፍቻ ቋንቋ እሴት ነው የሚባለው ቋንቋው በራሱ ባለው ዋጋ ብቻ ሳይሆን ተማሪው/ዋ በሌሎች ቋንቋዎች የቋንቋ እውቀትን/ግንዛቤን እና ሊተርሲን ለማሳደግ/ለማዳበር ስለሚጠቀምበትም/ስለምትጠቀምበትም ጭምር እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ።

የፌደራል እና የስቴት ህጎች ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች መቋቋም እንዲያስችላቸው እና እንደዚህ አይነት ተማሪዎች በትምህርት ፕሮግራም ላይ ሙሉ በሙሉ እንዳይሳተፉ የሚያግዷቸው መሰናክሎች እንዲወገዱ ለመርዳት የትምህርት ፕሮግራሞች፣ ድጋፎች፣ እና የተወሰኑ ማመቻቸቶች እንዲደረግላቸው ይደነግጋሉ። እነዚህም በሁለት ቋንቋ የሚሰጡ ግምገማዎች፣የካውንስሊንግ/የማማከር አገልግሎት፣እና ወላጆች/አሳዳጊዎች በእነርሱ/በተማሪዎቹ ምትክ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲሟገቱላቸው

የሚረዱ የወላጅ/የአሳዳጊ የድጋፍ አገልግሎቶችን የመሳሰሉ በሁለት ቋንቋ የሚሰጡ ትምህርቶችን እና አገልግሎቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

"EML/ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪ" ሁሉን አቀፍ/ሁሉንም የሚያጠቃልል ቃል ነው፤ ነገር ግን አንድ አይነት የሆኑ ሰዎች ያሉበት ቡድን አይደለም። EMLs/ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች ብዙ አገሮችን እና ቋንቋዎችን ይወክላሉ፤ እናም በቀድሞ የሕይወት ልምዳቸው፣ ቀጣይነት ባለው ወይም በተቆራረጠ ትምህርታቸው፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሊተርሲ ችሎታቸው፣ እና ወደ MCPS በገቡበት ዕድሜያቸው በስፋት ይለያያሉ።

C. **አቋም**

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ለጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች ድጋፍ ያለውን ቁርጠኝነት እንደሚከተለው ያረጋግጣል፦

    a) [ትኩረት/አጽንዖት እንዲሰጠው በማለት በፊት ከነበረበት ቦታ የተቀየረ] የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች አካዴሚያዊ ስኬት ተማሪዎቹ፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰቡ፣ እና ሁሉም አስተማሪዎች የሚጋሩት ኃላፊነት መሆኑን እውቅና መስጠት፣

    b) ከሁሉም ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ከሚጠበቁ ነገሮች ጋር በሚጣጣም መልኩ ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) በማዳመጥ፣ በመናገር፣ በማንበብ እና በመፃፍ ዘርፎች በአካዳሚክስ እና በማህበራዊ እንግሊዝኛ ቋንቋ የተሟላ ብቃትን እንዲያዳብሩ የሚያግዙ ውጤታማ የሆኑ እድሎችን መስጠት፣

    c) ቀደም ሲል በሌላ ቋንቋ የነበራቸውን የሊተርሲ ብቃት፣ ቀጣይነት ያለው ወይም የተቆራረጠ ትምህርት፣ የግንዛቤ ችሎታዎች፣ ወይም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸው እና ብቃታቸው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የግለሰብ ፍላጎቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) ተገቢውን ትምህርት መስጠት፣

    d) ለሁሉም ተማሪዎች የተዘጋጀውን እና ከሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቀውን አይነት ተመሳሳይ ከፍተኛ የትምህርት ውጤታማነት እንዲያሟሉ፣ እና ከሁሉም ተማሪዎች ከሚጠበቁ ደረጃዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ የንባብ እና የቋንቋ ስነጥበብ፣ የሂሳብ፣ የሶሻል ስተዲስ/የማህበራዊ ጥናት፣ የሳይንስ፣ የሙያ እና የቴክኖሎጂ ትምህርት፣ የኪነ ጥበብ፣ የጤና፣ እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርትን ጨምሮ በሁሉም የትምህርት ዘርፎች ፈታኝ የሆኑ MSDE የትምህርት እና የአፈጻጸም ደረጃዎችን እንዲያሟሉ ወይም ከዚያ ከፍ ያለ ውጤት እንዲያመጡ ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎችን (EMLs) ማዘጋጀት፣

    e) በአሁኑ ጊዜ ELD ፕሮግራሚንግ ለሚወስዱ ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) ትክክለኛ እና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የችሎታ ምዘናዎችን ማድረግ እና በፌደራል ህግ መሰረት ሊያገኙዋቸው የሚችሏቸውን ማመቻቸቶች ማቅረብ፣

    f) ELD ፕሮግራም ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በፌዴራል ህግ መሰረት የማግኘት መብት ያላቸውን የችሎታ ምዘና ማመቻቸት እና ትምህርታዊ ማመቻቸቶች ላይ ለሁሉም ሰራተኞች ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ትምህርት መስጠት።

2. የእንግሊዝኛ ቋንቋ የማዳበር (ELD) ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

    a) እያንዳንዱ ትምህርት ቤት፣ ከትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽህፈት ቤት "Office of School Support and Improvement" እና ከስርዓተ ትምህርት እና የትምህርት ፕሮግራሞች ጽህፈት ቤት "Curriculum and Instructional Programs" ጋር በመተባበር፣ እንደ

አስፈላጊነቱ፣ ለፕሮግራሙ ብቁ ለሆኑ ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) የተለያዩ ፍላጎቶች ምላሽ የሚሰጡ ELD ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን ይሰጣል/ያቀርባል።

b) ELD ስርዓተ ትምህርት –

(1) በጥናት ላይ የተመሰረተ፣

(2) ለእድሜ በሚመጥን አኳኋን የተዘጋጀ እንግሊዝኛን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ እና የመጻፍ ብቃት፣

(3) MSDE የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ካሉ የብቃት ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ፣

(4) MCPS የንባብ/የእንግሊዘኛ/የቋንቋ ስነጥበባትሥርዓተ ትምህርት የማንበብ እና የመጻፍ ዓላማዎች ጋር የተጣጣመ፤

(5) ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) የሚወክሏቸውን በርካታ የባህል እና የቋንቋ ዳራዎችን የሚያንፀባርቅ፣ እና

(6) ተማሪዎቹ MCPS ውስጥ ትምህርት ሲከታተሉ ለሚያጋጥማቸው የማስተማሪያ ስልቶች እና የትምህርት ዓይነቶች እና ይዘቶች የሚያዘጋጃቸውን የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚሰጥ ትምህርት ነው።

c) ተዛማጅ ELD ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

(1) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ቦርድ ፖሊሲ ABC፣ *የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ትብብርና አጋርነትጋር* በሚጣጣም መልኩ፣ MCPS በርካታ ስልታዊ በሆነ መንገድ የሚተገበሩ የትምህርት አቀራረብ ስልቶችን እና መሳሪያዎችን በመጠቀም ስለ ተማሪ ትምህርት እና እድገት መደበኛ፣ ትርጉም ያለው የሁለትዮሽ ግንኙነት ያደርጋል፣ ይህም ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) ወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪዎቻቸው ጥብቅ የሆነ ትምህርት እና ትምህርታዊ እድሎችን እንዲያገኙ አስፈላጊ ስለሆኑት ወሳኝ ትምህርታዊ መመዘኛዎችን/የችሎታ መለኪያዎችን፣ የኮርስ ቅደም ተከተሎችን፣የተማሪ አገልግሎት ትምህርት መስፈርቶችን እና እድሎችን፣የጊዜ ሰሌዳዎችን እና የማመልከት ሂደቶችን እንዲማሩ እድል ይሰጣቸዋል።

(2) EML ቴራፒዩቲክ አማካሪዎች/ካውንስለሮች ELD ፕሮግራም ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎችን በአዲሱ ትምህርት ቤታቸው እና በሚኖሩበት ማህበረሰብ አካባቢ ለመርዳት እንደ አግባብነቱ ለተማሪዎች የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ።

(3) አንድ ተማሪ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልገው እክል አለበት ተብሎ ሲጠረጠር፣MCPS ተማሪው(ዋ) በሚጠቀምበት/በምትጠቀምበት ዋና ቋንቋ

የግምገማ መሳሪያዎችን ይጠቀማል። አግባብነት ያለው የግምገማ መሳሪያ ተማሪው(ዋ) በሚጠቀምበት/በምትጠቀምበት ዋና ቋንቋ ከሌለ፣ መረጃው የእድገት ታሪክን፣ የትምህርት አቀባበል ታሪክን፣ የሊተርሲ እድገትን/ግስጋሴን፣ እና ቀስ በቀስ እያደገ የመጣውን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታን/ብቃትን በመመርመር/በማጥናት በርካታ ምንጮችን መሰብሰብ አለበት።

d) ለጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች የመማር-ማስተማር ፍላጎቶችን ለማሟላት የሰራተኞች የሙያ እድገት ጥራት ያለው ELD ፕሮግራም ዋና አካል ነው። ሙያን የማዳበር የትምህርት እድሎች በአሁኑ ጊዜ ELD ፕሮግራሚንግ እየወሰዱ ካሉ ወይም ከዚህ ቀደም ከወሰዱ ተማሪዎች ጋር ለሚሰሩ ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ይሰጣሉ።

3. ልየታ እና እንደገና መመደብ

a) የቋንቋ ችሎታ ምዘና ELD ፕሮግራም ብቁ የሆኑ ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎችን (EMLs) ለመለየት ጥቅም ላይ ይውላል፤ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃቸውን በሚከተለው መልኩ ይወስናል፦

(1) በፌዴራል መመሪያዎች የተደነገገ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ምዘና ብቃት ባላቸው እና በሰለጠኑ ግለሰቦች ይሰጣል።

(2) ምዘናው የሚሰጠው መጀመሪያ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በተመዘገቡበት ወቅት በፌደራል የሜሪላንድ የቤት ውስጥ ቋንቋ ዳሰሳ (HLS) ላይ ከሦስት ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱን ከእንግሊዝኛ ውጪ በሆነ ቋንቋ ለሚመልሱ ተማሪዎች በሙሉ ነው።

b) ELD ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች MSDE መመሪያዎች ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ሲያሟሉ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት ያላቸው እና በድጋሚ የተመደቡ/Reclassified ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) ተብለው ይመደባሉ።

c) ከ ELD ፕሮግራም የሚወጡ ተማሪዎች አፈጻጸም ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛ ቋንቋን ማዳበር ቡድን ክትትል ያደርጋል፣ እና ለሁለት ዓመታት ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል።

D. **የሚጠበቁ ውጤቶች**

1. ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሲወጡ በትምህርት ቤታቸው እና በማህበረሰባቸው ውስጥ እድገት ያሳዩ እና ስኬታማ የሆኑ ብቁ የእንግሊዝኛ ቋንቋ አንባቢዎች እና ጸሀፊዎች ሆነው ይወጣሉ።

2. ELD ፕሮግራም አገልግሎቶች ብቁ ለሆኑ ለሁሉም ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) ይሰጣሉ፤ እና በተማሪ የትምህርት ዳራ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃዎች ውስጥ ላሉ ልዩነቶች እውቅናን ባገናዘበ መልኩ ይዘጋጃሉ።

3. ELD ፕሮግራም ውስጥ ከሚሳተፉ እና ከፕሮግራሙ ከሚወጡ ተማሪዎች የሚጠበቀው የስኬት ደረጃ MCPS ውስጥ ካሉት ሁሉም ተማሪዎች ከሚጠበቀው የስኬት ደረጃ ጋር እኩል ተመጣጣኝ/የሚጣጣም ነው።

4. ትምህርቱ ተማሪዎች በተቻለ ፍጥነት እንግሊዘኛ እንዲማሩ ያስችላቸዋል፣ በተመሳሳይ በትምህርት ይዘት ከክፍል ደረጃ እኩዮቻቸው ወደ ኋላ እንዳይቀሩ ይረዳቸዋል።

5. MCPS ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎችን (EMLs) በበርካታ ቋንቋዎች የመግባባት ችሎታ እና በሌሎች ቋንቋዎች ሊተርሲ ለመቻላቸው እንዲሁም ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) ለመማሪያ ክፍሎች እና ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ ለሚጨምሩት የቋንቋ እና የባህላዊ እሴቶች ዋጋ ይሰጣል።

E. **የአተገባበር ስልቶች**

የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ የሚከተሉትን ያደርጋል/ታደርጋለች –

1. MCPS ውስጥ ላሉ ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች ተገቢ የሆኑ ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት፣ ለማስቀጠል እና ለመገምገም አስተዳደራዊ ሂደቶችን/አሠራሮችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፤

2. ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ተደራሽ የሆኑ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ተመሳሳይ የትምህርት እድሎችን እንዲያገኙ ከዚህ ቀደም ELD ፕሮግራሚንግ የወሰዱ ወይም በአሁኑ ጊዜ ፕሮግራሚንጉን የሚወስዱ ተማሪዎችን ለመደገፍ ከሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተማሪዎች የሚጠበቁትን የጋራ ሀላፊነቶችን በግልፅ ያስቀምጣል/ታስቀምጣለች።

3. ELD ተማሪዎች ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ተደራሽ የሆኑ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ተመሳሳይ የትምህርት እድሎችን እንዳያገኙ ቋንቋ እንቅፋት እንዳይሆንባቸው የአሁን እና የቀድሞ ELD ተማሪዎችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ስለመደገፍ መመሪያ ያወጣል።

4. በ MSDE መመሪያዎች መሰረት፣ELD የፕሮግራም መለያ እና የፕሮግራም ማጠናቀቂያ ሂደቶችን/አሰራሮችን እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው ይገመግማል/ትገመግማለች እና ይከልሳል/ትከልሳለች፤

5. በአሁኑ ወቅት ELD ፕሮግራሚንግን የሚወስዱ ተማሪዎች ያሏቸውን በሰነድ የተቀመጡ/የቀረቡ ፍላጎቶችን መሰረት በማድረግ እና ባለው የበጀት አቅም መሠረት ሰራተኞችን እና የቁሳቁስ መገልገያዎችን/ሪሶርሶችን በየዓመቱ ውጤታማ በሆነ መልኩ ይመድባል/ትመድባለች፣

6. ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ተገቢ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ከፌዴራል ለማግኘት ያመልክታል፤ እና

7. ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) እና ቤተሰቦቻቸው የሚያስፈልጓቸውን መገልገያዎች/ሪሶርሶች እንዲያገኙ ለማመቻቸት ከካውንቲ ኤጀንሲዎች እና ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ይተባበራል/ትተባበራለች።

F. **ግምገማ እና ሪፖርት**

1. በየዓመቱ፣ የአሁን እና የቀድሞ ELD ፕሮግራም ተሳታፊዎች አካዴሚያዊ ግስጋሴን/እድገትን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ በዓመታዊ ዘገባ ሪፖርት ያደርጋል/ታደርጋለች።

2. MCPS ለአሁን እና ለቀድሞ ELD ፕሮግራም ተሳታፊዎች ሁሉንም የፌደራል እና የስቴት ሪፖርት የማድረጊያ መስፈርቶችን አሟልቶ ይተገብራል።

3. ይህ ፖሊሲ የሚገመገመው በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት ነው።

የፖሊሲው ታሪክ:- ውሳኔ ቁጥር 77-80 ጃንዋሪ 21,1980 በውሳኔ ቁጥር 333-86 ጁን 12,1986 ተሻሽሏል፣በውሳኔ ቁጥር 599-99 ኦክቶበር 14,1999 ተሻሽሏል፣ የተሻሻሉ የጽ/ቤት ስያሜዎች ጁን 1, 2000፣ ሴፕቴምበር 13, 2011 በውሳኔ ቁጥር 450-11 ተሻሽሏል፣ በውሳኔ ቁጥር 302-24 ጁን 11, 2024 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኸውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

<table>
<tr><td>በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td><td>በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>1973 የተሃድሶ ድጋፍ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 | 504@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org